*ጋዜጣዊ መግለጫ*


ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው

የአሜሪካ ኤምባሲ፤ ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033

አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ ድረገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov


2014/33

---

## የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ የልዩ ቡና ገበያን ለማሳደግ የቡና ጥራት ላቦራቶሪ መሣሪያዎችን ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ አበረከተ

ሐዋሳ፤ደብብሕክ፤ኢትዮጵያ፤መስከረም 27፣2007፡- የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ የግብርና ምርት አቅርቦት ማሳደጊያ መርሀ ግብር የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የልዩ ቡና ጥራት የሚያረጋግጥባቸውና በአሜሪካ የልዩ ቡና ጥራት ማረጋገጫ ማኅበር የሚፈለገውን ዕውቅና ለማግኘት በሐዋሳ፣በጅማና በዲላ ለሚገኙ ላቦራቶሪዎች የሚውሉ የተለያዩ መሣሪያዎችን አበረከተ፡፡

ቡና የኢትዮጵያ ዋንኛ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የምርቱን ጥራትና ተቀባይነት ለማሳደግ የተለያዩ ስልቶችን ቀርጾ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ የዚህን የቡና ገበያ ማስፋፊያ እንቅስቃሴ ለመደገፍ የአሜሪካ መንግሥት ለናሙና ምርመራና ለደረጃ ምደባ የሚያገለግሉ አዳዲስ መሣሪያዎችን 3.3 ሚሊዮን ብር/ 175፣000 ዶላር ወጪ በማድረግ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ አበርክቷል፡፡ መሣሪያዎቹ የቡና መፍጫና መቁያ ማሽኖችን የሚያጠቃልሉ ሲሆኑ፤ እርጥበትን ለመለካት፣የሙከራ ናሙናዎችን ለማዘጋጀትና ሌሎች የድርጅቱን አሠራር ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያግዙትን ይጨምራል፡፡ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ የግብርና ምርት አቅርቦት ማሳደጊያ መርሀ ግብር የላቦራቶሪ አገልግሎት የሚሰጡባቸው ህንፃዎች በአሜሪካ የአካባቢው ቡና ጥራት ማረጋገጫ ማኅበር መስፈርት መሠረት እንዲዋቀሩና እንዲታደሱ አድርጓል፡፡

ለላቦራቶሪዎቹ እነዚህን መሣሪያዎች ማቅረብና በአሜሪካ የልዩ ቡና ጥራት ማረጋገጫ ማኅበር ዕውቅና እንዲያገኙ ማመቻቸት ዓለም አቀፉ የቡና ምርት ገበያ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ላቦራቶሪዎች በምርጥ አሠራር ላይ የተመሠረቱና ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ናቸው በሚል እንዲተማመን ያደርጋል፡፡ በቀጥታ ከገበሬ ህብረት ሥራ ማህበራት ምርት የሚረከቡ ገዢዎችም፤ በቡናው ደረጃ ያላቸው መተማመንም ከፍ ያለ ይሆናል፡፡ ይህም ሲሆን የህብረት ሥራ ማህበራቱ አባላት ምርቶቻቸውን ከፍ ባለ ዋጋ መሸጥና ለአባላቶቻቸው ላቅ ያለ ገቢ ማስገኘት ይችላሉ ማለት ነው፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ አራቢካ በተሰኘው የቡና ዝሪያ አምራችነት በሦስተኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ ሲሆን፤ በአፍሪካ ደረጃ በ2005 ዓ.ም. የአሜሪካ የልዩ ቡና ጥራት ማረጋገጫ ማኅበር ዕውቅናን በማግኘት በአፍሪካ የመጀመሪያዋ አገር ለመሆን በቅታለች፡፡

በዚህ ዓመትም በነዚህ አምስት የጥራት ማረጋገጫ ላቦራቶሪዎች አማካይነት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል ጥራቱ እየተረጋገጠ ወደ ውጭ የሚላከው ከፍተኛ ጥራት ያለው የቡና መጠን እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ከንግድና ከግብርና ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ከኢትዮጵያ የምርት ገበያ ጋር በቅርበት በመሥራት ለገበሬዎች ህብረት ሥራ ዩኒየኖች አባላትና ለባለ አነስተኛ ይዞታ ገበሬዎች ድጋፍ ያደርጋል፡፡

*በአሜሪካ አለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ የሚመራው የግብርና ምርት የገበያ አቅርቦት ማሳደጊያ ፕሮግራም በኢትዮጵያ የሚተገበረው መጪውን ትውልድ መመገብ (Feed the Future Initiative) የተሰኘ መርሀ ግብር ዋና አካል ሲሆን የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ለኢትዮጵያ መንግሥት የግብርና ዕድገት መርሀ ግብር ከሚያደርገው ድጋፍ ትልቁን ድርሻ የሚይዝ ነው፡፡*